# የጠ/ሚኒስትር መለስ ደጋፊዎች ሰልፍ ምን መልዕክት ያስተላልፋል?

ከንጉሴ ጋሻ

የድጋፍም ሆነ የተቃዉሞ ሕዝባዊ ስብሰባና ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ የሰዉ ልጆች ዲሞክራሲያዊ እና ሰብዓዊ መብት እንደሆነ ለማንም ግልፅ ነዉ። አንድ አገራዊ ጉዳይን በሚመለከት በተመሳሳይ ቀንና ስፍራ በቅርብ ርቀት የሚደረጉ የድጋፍና የተቃዉሞ ሰላማዊ ሰልፎች ግን አንዱ ለሌላይኛዉ ዓላማ ያለዉን ተቃዉሞ ከመግለፅና የሚዲያ ሽፋን ለማግኘት ከመሻት ባሻገር አመፅ በማይታይበት መልክ ተሰላፊዎቹ በሚወክሏቸዉ ህዝቦችና አባላት መካከል ግጭት ለመፍጠር የሚደረግ ጥረት ነዉ።

አብዛኛዉን ጊዜ እንደዚህ ዓይነት ግጭት ለመጫር የሚጠነሰሱ ሕዝባዊ ስብሰባዎችና ሰልፎች የሚደረጉት በራሳቸዉ የማይተማመኑ ሃይሎች በተለይም የመንግስትና የድርጅት መሪዎች ከጀርባ በመሆን በሚያደርጉት ሁሉን አቀፍ ድጋፍ እንደሆነ ግልፅ ነዉ።

ስለሆነም ባለፈዉ ነሐሴ 3 ቀንና ባለፈዉ መስከረም 22 ቀን 2010 በይናይትድ ሰቴትስ የጠ/ሚኒስትር መለስ ደጋፊዎች ያደረጉት ሰልፍ በማን እና ለምን እንደተደረጉ ለማወቅ ነቢይ መሆን አያስፈልግም። በኢትዮጵያ ያለዉ የወያኔ/ ኢህአዴግ መንግስት ጠባብ ዘረኛ መሪዎች ከጀርባ ሆነዉ በዚያ በሚገኘዉ የኤምባሲ ጽ/ቤት አማካይነት ያቀነባበሩት እንደሆነ ግልጽ ነዉ።

ወያኔ/ኢህአዴግ ዘመን ባለፈበት በከፋፍለህ ግዛዉ ፖሊሲ በመጠቀም ለሆዳቸዉ በሚገዙ ደካማ ወገኖች በመጠቀም እዉነተኛ ተቃዋሚ የሆኑትንና ለአምባገነን አገዛዙ ሊያጎበድዱ በማይፈልጉት የፖለቲካ ፓርቲዎችና የሲቪል ማህበራት ምትክ በአምሳሉ ጠፍጥፎ በመፈልፈል ለዲሞክራሲ የሚታገለዉን የተቃዋሚ ጎራ ለማዳከም ሲፈፅም የነበረዉን ወንጀል የሚያዉቅ ሁሉ ይህ የጠ/ሚኒስትር መለስ ደጋፊዎች ሰልፍ እንዴት ሊቀነባበር እንደቻለ በሚገባ ይረዳዋል።

ይህ አሁን በዚህ ሁለት አጋጣሚዎች የታየዉ የጠ/ሚኒስትር መለስ ደጋፊዎች ሰልፍ በአገር ቤት ሲካሄድ የነበረዉ የተቃዋሚ ሃይሎች ጎራን የመፍጠር የወያኔ/ኢህአዴግ ቀጣይ ተግባር ነዉ። የግንቦት 1997 ብሄራዊ ምርጫን ሽንፈት ተከትሎ ወያኔ/ኢህአዴግ በግንባር ቀደምትነት የያዘዉ አጀንዳ በዉጭ አገር ያለዉን

ተቃዋሚ ኢትዮጵያዊ በተቻለ መንገድ በቤት መስሪያ የከተማ ቦታ፡ በኢንቬስትሜንት ፈቃድና በሌሎች ጥቅማ ጥቅም አፉን ማዘጋት ካልተቻለም በእንዲህ ዓይነቱ ስልት በመንቀሳቀስ መቆጣጠር እንደሆነ ከኢትዮጵያ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሾልኮ የወጣዉ 52 ገፅ ሚስጥራዊ ሰነድ በግልፅ አስፍሮታል።

በዉጭ የሚገኙት የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና የቆንሱላ ጽ/ቤቶች እስከ 2016 ድረስ የዜጎቻቸዉን መብት፡ ሰላምና ደህንነት ማስከበር ሳይሆን ዋነኛ ተግባራቸዉ በዉጭ አገር ያለዉ ኢትዮጵያዊ በአገሩ በመካሄድ ላይ ያለዉን የሰብዓዊ መብት ረገጣና አምባገነኑ የጠ/ሚኒስትር መለስ መንግስት በሁሉም ዘርፍ ከህግ በላይ በመሆን በወገኖቹ ላይ የሚፈፅመዉን ወንጀል ለዓለም ሕብረተሰብ እንዳያጋልጥ ለማድረግ አጣዳፊ የደህንነት ስራ መስራት እንደሆነ ግልፅ ነዉ። ይህንን ተግባር ሃላፊነት በመዉሰድ እንዲያከናዉን በዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዉስጥ የዳያስፖራ መምሪያ መቋቋሙ ይታወቃል።

እዚህ ላይ አንድ ግልፅ መሆን ያለበት ጉዳይ ቢኖር በዲሞክራሲያዊ መንገድ ድጋፍ ማድረግ እንችላለን ብለዉ የሚገምቱ ሃይሎች ዲሞክራሲያዊ መብታቸዉ እስከምን ደረጃ መሆን እንዳለበት ጠንቅቀዉ ያለማወቃቸዉ ነዉ። በዲሞክራሲያዊ አገር ዉስጥ እየኖሩ የህዝቦች ዲሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች ይከበሩ፡ የሕግ የበላይነት ይከበር ፡ ግልፅነትና ተጠያቂነት ይኑር፡ የሚሉ ሌሎች ወገኖችን ለመቃወም መዉጣት በራሱ ወንጀል እንደሆነ መገንዘብ በቅደሚያ ተገቢ ነዉ።

ጠ/ሚኒስትር መለስ እና ዘረኛ ጠባብ የፖለቲካ ፓርቲያቸዉ ሰብዓዊና ዲሞክራሲአዊ መብቶችን እንዲረግጡ፡ በአገሪቱ ላይ የህግ የበላይነት እንዳይከበር በማለት ወንጀል እንዲፈፀም የሚጠይቅ የሰልፍ ዓላማ ይዘዉ አደባባይ መዉጣታቸዉን የተረዱት አይመስልም። ትናንት በጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ትዕዛዝ በአግኣዚና በፌዴራል ፖሊስ ወታደሮች በግፍ ወንድሙ፡ እህቱ፡ ቤተሰቡ የተገደለበት ፡ አባቱ፡ እናቱ አጎቱና አክስቱ በዚህ ሰዓት በቃሊቲ፡ በሸዋ ሮቢት በደንቆሮ ጫካና በሌሎችም የአገሪቱ እስር ቤቶች ከሕግ ዉጭ የታሰረበት፡ የቅርብም ይሁን የሩቅ ዘመዱ ከስራዉ ተፈናቅሎ፡ ቤት ንብረቱን በሃይል ተነጥቆ በረሃብና በስቃይ የሚንገላታበት ኢትዮጵያዊ ዜጋ ባለበት የወያኔ/ኢህአዴግ ደጋፊዎች በዲሞክራሲያዊ አገር ዉስጥ አጠገቡ ፊንጠር ብለዉ ቆመዉ፡" ደግ አደረግህ መለስ፡ እርገጥ፡ እሰር፡ ግረፍ፡ ግደል፡ ንጠቅ ፡" እያሉ ሲገፉፉት፡

በዲሞክራሲ ስም ሲጨፍሩበትና አንገቱን ለማስደፋት ሲሞክሩ ምን ሊሰማዉ፡ አይቶ ጠብቆ ፡ስሜቱን መቆጣጠር ሲሳነዉ በአፀፋዉ ሊወስድ የሚችለዉ የምሬት እርምጃ እንደምን እንደሰዉ ሊታሰባቸዉ አይችልም? ስሜቱን መቆጣተር የተሳነዉ በሁኔታዉ ተገፋፍቶ ሊወስድ በሚችለዉ እርምጃ የጥፋቱ ዝርዝር በፍርድ ሂደት ሊኖረዉ የሚችለዉን የሕግ አፈፃፀም አለመረዳት ትልቅ ድክመት ነዉ።

የጠ/ሚኒስትር መለስ ደጋፊዎች ሰልፍ የሚያስተላልፈዉ መልዕክት ብዙ ነዉ።

በመጀመሪያ ደረጃ ደጋፊዎቹ የዲሞክራሲ ምንነት በግልፅ ያልገባቸዉ ከራሳቸዉ ጥቅም በላይ አሻግረዉ ማየት የተሳናቸዉ መሆናቸዉን ያስገነዝባል።

በሁለተኛ ደረጃ ሕዝብ በአምባገነንነት የፈረጀዉን ነፍሰ ገዳይ "ደግ አደረግህ፡ ግፋ ቀጥልበት" ብሎ ሌላ ወንጀል በወገን ላይ እንዲፈፅም በግልፅ መገፋፋት በእራሱ ወንጀል መሆኑ አልታሰባቸዉም። የጀርመን የአምባገነንነትና የበላይነት ወቅት በተባበሩት ሃይሎች ህብረት ሲገረሰስና ሲወድቅ፡ ንፍሰ ገዳዮቹ በኑረምበርግ ለፍርድ ሲቀርቡ ጠመንጃ ያነገቡና ጥይት የተኮሱ ወታደሮች ብቻ ሳይሆኑ በችሎት ሳጥን ዉስጥ የቆሙት በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ናዚ ፋሽስቶችን ትክክለኛ አድርገዉ በያጋጣሚዉ ድምፃቸዉን ያሰሙ ደጋፊዎቻቸዉ ሁሉ ነበሩ።

በሶስተኛ ደረጃ የመለስን የአምባገነንነት ገፅታ ለመቀየር እነዚህ በተለያየ መንገድ የተገዙ ሃይሎች አጉል ይፍጨርጨሩ እንጂ የዓለም አቀፉ ሕብረተሰብ በተለይም ዩናይትድ ስቴትስና ሌላዉ የምዕራቡ ዓለም ዛሬ ወያኔ/ኢህአዴግ ቅጥር አገልጋያቸዉ በመሆኑ እያዩ እንዳላዩ ይለፉት እንጂ ከህወሃት ጀሌዎች ይበልጥ ህወሃትን በሚገባ ያዉቁታል፡በሕዝቧና በአገሪቱ ሉዓላዊነት ላይ በእብሪት በገሃድና ዉስጥ ለዉስጥ በሚስጥር የሚፈፅመዉን እያንዳንዱን ጥቃቅን ነገር ጠንቅቀዉ ይረዱታል፡ ይመዘግቡታል።

በዲሞክራሲአዊ አገር ዉስጥ "ደግ አደረግህ መለስ፡" ብለዉ የተሰለፉ ደካሞች በአገር ቤት ቢሆኑና ሕዝብ በመንግስት ላይ ቢነሳ በፍልሚያዉ ጣልቃ ከመንግስት ጎን ተሰልፈዉ ህዝብን የሚጨፈጭፉ መሆናቸዉን አሌ ማለት አይቻልም።

በሰላማዊ መንገድ ችግሮችን ለመፍታት ፈቃደኛነት የጎደለዉን መንግስት "ዲሞክራዊያዊ በሆነ መንገድ በህዝብ የምርጫ ድምፅ ስልጣኔን በሰላማዊ መንገድ አሳልፌ አልሰጥም። ህወሃት ከስልጣን ከተወገደ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገርና ህዝብ አይኖርም ፡ አገሪቱ የሩዋንዳ ዕጣ ይገጥማታል" በማለት ጠ/ሚኒስትር መለስና

ፓርቲያቸዉ ዘወትር የሚያሰሙት የመጠፋፋትና የዘር ጭፍጨፋ አራማጆች እንደነዚህ ያሉት ግለሰቦች እንደሆኑ ከወዲሁ ለሁላችንም ግልፅ እየሆነ ነዉ።
መለስ ለአገዛዛቸዉ እንዲመች ሲያስተጋቡ የነበረዉ የርስ በርስ እልቂት የመጀመሪያ አመላካቾች መሆናቸዉን ከወዲሁ ሁሉም ልብ ሊለዉ ይገባል። ለዚህ ደግሞ ብቸኛዉ ምልክት ለሰልፋቸዉ ድምቀት እንደ ጥሩምባና ፊሽካ እንዲያገለግሉ በዕቃነት ከሚጠቀሙባቸዉ ሰሎሞን ተካልኝና ጥቂት ቢጤዎቹ ዉጭ አደባባይ የወጡት የጠ/ሚኒስትር መለስ ደጋፊዎች ሙሉ በሙሉ ማለት ይቻላል የትግራይ ተወላጆች መሆናቸዉ አጠቃላይ አዝማሚያዉ ወዴት እየሄደ እንደሆነ በራሱ የሚያስተላልፈዉ መልዕክት አለ።
ይህ የሚያሳየዉ ከ80% ብሄር ብሄረሰቦች በሚገኙባት አገር ከ4-6% የሚሆነዉ የአንድ ብሄረሰብ አባላት አገሪቱን ኢዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ በአምባገነንነት በሃይል ተቆጣጥረዉ በበላይነት እንዲያስተዳድሩ ለማስገደድ የሚደረግ ዓይን ያወጣ ፍጥጫ ነዉ።
የመንግስት የስልጣን ጥያቄ ሕገ መንግስታዊና ዲሞክራሲያዊ በሆነ በሰላማዊ መንገድ በሕዝብ ድምፅ መመለስ ሲገባዉ የታሪክ፣ የባህል፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ትስስር ያለዉን አንድ ሕዝብ በዘርና፣ በጎሳ በመከፋፈል አላስፈላጊ በሆነ ደም መፋሰስ ለመቆጣጠር ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ዘወትር የሚያቀነቅኑትን የኢንተርሃምዌን ዜማ ተቀብሎ ማቀንቀን፣ የርስ በርስ ዕልቂት አታሞ መደለቅና በስመ ዲሞክራሲ ድጋፍ በእብሪት ለጥፋት መነሳት ትልቅ የታሪክ ስህተት እንደሆነ መገንዘብ ይበጃል።
አገር ቤት ያለዉ ሁኔታ እስከሚፈቅድ ድረስ አንዴ እንደሁ እዚያ የሚገኘዉ ወገን መብቱን በአምባገነኖች ተገፏል፣ በዉጭ ያለዉ ወገን ግን በዲሞክራሲያዊ ስርዓት ዉስጥ እንዳለ ለእንደዚህ ዓይነቶቹ አጨብጫቢዎች ጊዜዉ ሳይመሽ ግልፅ ሊሆንላቸዉ ይገባል።
አገር ቤት ዘመዱ የተገደለበትን፣ አላግባብ ወህኒ የተጣለበትን ሌላ ሌላም ጉዳት የደረሰበትን ቁስሉን እየነካኩ ማን ይነካናል ብሎ በእብሪት መሰለፍ መዘዙ የከፋ ሊሆን እንደሚችል ቆም ብሎ ማሰብ ይጠቅማል። ይህቺ ሽምብራ ያደረች እንደሆን…… የሚሉት የአበዉ አባባል እዉነትነት አለዉ ጎበዝ…